# በፌደራል ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር
# የኢትዮጵያ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
# ዜና ኢ.ሕጤኢ.

ሚያዝያ 2008 ቅጽ 1 ቁጥር 7

በኢ.ሕጤኢ. የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ቢሮ በየወሩ የሚዘጋጅ


## ኢንስቲትዩቱ የሁለተኛውን ዙር የህዝብ ክንፍ ውይይት አካሄደ



የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የበጀት አመቱን ሁለተኛ ዙር የህዝብ ክንፍ ስብሰባ ሚያዚያ 26/2008 ዓ.ም የተለያዩ ተቋማት ተወካዮች በተገኙበት በኢንስቲትዩቱ አዳራሽ  ውይይት አካሂደ፡፡

በስብሰባው ላይ  የተገኙት የኢትዮጵያ እንሰሳት ህክምና ማህበር፣የኢትዮጵያ  ህብረተሰብ ጤና ላብራቶሪ ማህበር፣ የኢትዮጵያ የምግብ ሳይንስና ኒውትሪሽን ባለሞያዎች ማህበር፣የምግብ አምራቾች ማህበር፣የጉለሌ ክ/ከተማ ወጣቶች ማህበር፣ኔትዎርክስ ኦፍ ኤች አይ ቪ. ፖዘቲቭ፣ የኢትዮጵያ ፋርማሲስት ማህበር እና የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና አጠባበቅ ማህበር ናቸው፡፡

የስብሰባውን የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት ዶክተር ይበልጣል አሰፋ የኢንስቲትዩቱ ምክትል ዋና ዳይሬክተር  ስብሰባውን  አስመልክቶ እንደገለጹት ሃገራችን ኢትዮጵያ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ተርታ ለ

. . .ወደ ገጽ 3 ዞሯል

## ኢንስቲትዩቱ ጨቅላ ህጻናት ላይ የኤች አይ ቪ ምርመራ ለማካሄድ የሚያስችል ስልጠና ሰጠ




የኢትዮጵያ  ህብረተስብ  ጤና  ኢንስቲትዩት የኤች አይ ቪ. ሞሎኪዩላር ላብራቶሪ የጨቅላ ህጻናትን ኤች አይ ቪ. ምርመራ በቀላሉ ለማድረግ የሚረዳውን ኮባስ አምፕሊ. ፕሪፕታግማን የተባለውን መሳሪያ ግልጽ ለማድረግ ከሚያዚያ 3-9/2008 ዓ.ም ከተለያዩ 6 ሆስፒታሎች ተመረጠው ለመጡ 9 ባለሞያዎች ስልጠና ሰጠ፡፡

> ....የጨቅላ ህጻናትን ኤች አይ ቪ. ምርመራ በቀላሉ ለማድረግ የሚረዳ በቅርብ ጊዜ ወደሃገራችን የገባውን መሳሪያ.....

ወ/ሮ ቅድስት ዘኤልያስ የኤች አይ ቪ. ሞሎኪዩላር ላብራቶሪ ሃላፊ የስልጠናውን ዋና አላማ  እንደገለጹት የጨቅላ ህጻናትን ኤች አይ ቪ. ምርመራ በቀላሉ ለማድረግ  የሚረዳ በቅርብ ጊዜ ወደሃገራችን የገባውን መሳሪያ በስራ ላይ ከመዋሉ በፊት ባለሞያዎችን በሚገባ አሰልጥኖና አሳውቆ ወደ ስራው ለማስገባት ታስቦ የተዘጋጀ ስልጠና ነው ብለዋል፡፡

ሃላፊዋ  አያይዘው  እንደገለጹት  ስልጠናውን ሮሽ ከሚባለው የውጪ ካምፓኒ ጋር በጋራ በመሆን እየሰጠን ሲሆን ሰልጣኞች መሳሪያውን ከአገኙ ከጅማ ዩንቨርስቲ ሆስፒታል፣ከፖሊስ ሆስፒታል፣ከደብረብርሃን  ሆስፒታል፣ ከጎንደር ዩንቨርሲቲ ሆስፒታል ፣ከደብረ ማርቆስ ሆስፒታል እና ከኢትዮጵያ  ህብረተሰብ  ጤና ኢንስቲትዩት ተመርጠው የመጡ  ባለሞያዎች  ናቸው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ከስልጠናው በኂላ የኤች አይ ቪ. ሞሎኪዩላር ላብራቶሪ ቲም ከሰለጠኑት ባለሞያዎች ጋር በተጠቀሱት ሆስፒታሎችና ዩኒቨርሲቲዎች  ባሉበት ቦታ በመገኘት ስራውን በሚገባ እንደሚያስጀምሩ ሃላፊዋ ጨምረው አብራርተዋል፡፡

# የአጣዳፊ ምጥ እና የጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የዳሰሳ ጥናት ተጀመረ

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲ
ትዩት ከአጣዳፊ ምጥ እና ከእርግዝ
ና ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የተለ
ያዩ ችግሮችንና የጨቅላ ህጻናት ጤ
ና አገልግሎት አሰጣጥ ወቅታዊ ተ
ደራሽት፣ተጠቃሚነትና ጥራት ምን
እንደሚመስል ለማወቅ በሃገር አቀፍ
ደረጃ የዳሰሳ ጥናት ለማድረግ የመስ
ክ ባለሞያዎችን ሚያዚያ 25/2008
ዓ.ም የሽኝት ፕሮግራም አካሄደ።
ፕሮግራም መዘጋጀቱን ተናግረዋል።
ዶክተር አመሃ ከበደ የኢንስቲትዩቱ
ዋና ዳይሬክተር በበኩላቸው የደሰሳ
ጥናቱን ዋና አላማ እንደገለጹት አጣ
ዳፊ ምጥ፣ ከእርግዝና ጋር ተያያዥ
ነት ያላቸውን የተለያዩ ችግሮችንና
የጨቅላ ህጻናት ጤና አገልግሎት አ
ሰጣጥ ወቅታዊ ተደራሽት፣ተጠቃሚ
ነትና ጥራት ሁኔታ በሃገር አቀፍ ደ
ረጃ ለማየት ታስቦ የተዘጋጀ የዳሰሳ
ነው ብለዋል።
ዋና ዳይሬክተሩ በማጠቃለያቸው ላ
ይ እንዳስቀመጡት የዚህን የዳሰሳ
ጥናት ሃላፊነት የሚወስዱት የኢት
ዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት
ና ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር እንዲሁም
አጋር ድርጅቶች ናቸው ነገር ግን
ውጤቱ በእናንተ በመስክ ባለሞያዎ
ች ላይ የተወሰነ ስለሆነ መረጃውን
በሚገባ ጥራት ባለው መንገድ ልት



ሰበስቡ ይገባል በተቋሙ በኩል ግን
ለሚገጥማችሁ ችግር ሁሉ አፋጣኝ
መፍትሄ ለመውሰድ ዝግጅቱን አጠ
ናቋል ሲሉ ተናግረዋል።
በመጨረሻም የመስክ ባለሞያዎቹ
የተሰጣቸውን ሃላፊነት በሚገባ እንደ
ሚወጡ ቃል የገቡ ሲሆን አጠቃላ
ይ የመታሰቢያ የፎቶ ፕሮግራም ከ
ተቋሙ ከፍተኛ ሃላፊዎች ጋር በማ
ካሄድ የእለቱ የሽኝት ፕሮግራም ተ
ጠናቋል።

የሽኝት ስነ-ስረአቱም የተካሄደው የ
ተቋሙ ከፍተኛ ሃላፊዎች በተገኙበ
ት ነበር።
አቶ አበበ በቀለ የስርዓተ ጤና ምር
ምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ጥና
ቱን አስመልክቶ እንደገለጹት የዳሰሳ
ጥናቱን ውጤታማ ለማድረግ የመስ
ክ ባለሞያዎችን ለሁለት ሳምንታት
በሐዋሳ ከተማ በገለጻና በተግባር በ
ማስደገፍ የማሰልጠን ስራ መሰራቱ
ንና ባለሞያዎቹን የመስክ መረጃ እን
ዲሰበስቡ ለማድረግ የእለቱ የሽኝት
ጥናት ነው ብለዋል።
ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘው እንደገለጹ
ት ከጥናቱ የሚጠበቁ ዋና ዋና ው
ጤቶች የመሰረታዊ እና ሁሉ አቀፍ
የአጣዳፊ ምጥ፣ከወሊድ ጋር ተያያ
ዥ ችግሮች እና የጨቅላ ህጻናት ጤ
ና አገልግሎት ተደራሽት ማወቅ፣ሽ
ፋኑን በተመለከተ በወረዳ፣በዞን፣በክ
ልል እና አጠቃላይ በሃገር አቀፍ ደ
ረጃ መዳረሱን የማወቅ እና በእቅ
ድ የተያዘው ግቡን መቷል አልመ
ታም የሚለውን የምንለካበት ጥናት

# ጤናማ አመጋገብን ለማሻሻል እና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ የዳሰሳ ጥናት ተጀመረ

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጠና ኢን
ስቲትዩት የምግብ ሳይንስና ኒው
ትሪሽን ምርምር ዳይሬክቶሬት ያ
ልተመጣጠነ የአመጋገብ ስርአት
ችግርን በሃገር ደረጃ ለመቅረፍ
ሚያዚያ 3/2008ዓ.ም ጀምሮ ከ
አራት ክልሎች ለተመረጡ የዳሰ
ሳ ጥናት መረጃ ሰብሳቢ ባለሞያ
ዎች በኢንስቲትዩቱ አዳራሽ ስል
ጠና ሰጠ።
የስልጠናው ዋና አላማ በዘላቂነት
አቀንጭራነትን በሃገር ደረጃ በመ
ቀነስ በተለይም ከ5 ዓመት በታች
ላሉ ህጻናት ጤናማ አመጋገብ ለ
ማሻሻል እና በምግብ ያለመመጣ
ጠን ችግር ምክንያት የሚፈጠሩ
የተለያዩ ችግሮችን ለማጥፋት ታ
ስቦ የተዘጋጀ ስልጠና ነው።
የኢንስቲትዩቱን ዋና ዳይሬክተር
ን በመወከል የስልጠናውን የመክ

. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የኢንስቲትዩቱ ጡረተኞች ማህበር ተመሰረተ

በኢንስቲትዩቱ ለረጅም ጊዜ ሲያገለ
ግሉ የቆዩ የተለያዩ ባለሞያዎች የረ
ጅም ጊዜ ልምዳቸውንና እውቀታቸ
ውን ለኢንስቲትዩቱ ሰራተኞች ለማ
ካፈል በኢንስቲትዩቱ ስም የአገልግ
ሎት ማህበር  መሰረቱ።

አቶ አሰፋ መንግስቱ የማህበሩ ሰብ
ሳቢ የማህበሩን ምስረታ ዋና አላማ
እንደገለጹት ጡረታ የወጡ የተቋሙ
ሰራተኞች በተቋሙ ስም በማህበር
በማደራጀት ከመንግስት በሚደረገው
ከፍተኛ ድጋፍ በሞያቸው ስራዎች

ን እንዲሰሩ ለማድረግና በጡረተኛ ስ
ም የሞራል ውድቀት እንዳይፈጠር
ባቸው እንዲሁም ከተቋሙ ጋር ያላ
ቸው የግንኙነት ሰንሰለት እንዳይቋረ
ጥ በአእምሮ፣ በሞያ እና በጉልበት



. . .ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## . . . . .የህዝብ ክንፍ ስብሰባ

ከገጽ 1 የዞረ

ማሰለፍ በሁሉም ተቋም ጥረት እ
የተደረገ ይገኛል  ይህ ደግሞ ሊሳ
ካ የሚችለው በህዝብ  እና በተቋ
ማት መካከል ጥብቅ የሆነ ግንኙነ
ት ሲኖር ነው በመሆኑም ኢንስቲ
ትዩታችን  የበለጠ ውጤታማ እን
ዲሆን የዛሬውን የሁለተኛ ዙር ስ
ብሰባ አድርገናል ብለዋል፡፡
ም/ዋና ዳይሬክተሩ አያይዘው እን
ደገለጹት በዚህ መድረክ በተቋማ
ችንና በህዝቡ ክንፍ መካከል የጋ
ራ እቅድ የምናወጣበት፣ኢንስቲት
ዩቱና የህዝብ ክንፉ የተሰጣቸውን
ሃላፊነት በትክክል እየተወጡ ለመ
ሆናቸው የምንገመግምበት፣የተሰራ
ና ያልተሰራውን ተግባር በመለየ
ት ያልተሰራበትን ምክንያት የም
ንፈትሽበት ስለሆነ መድረኩ እጅ
ግ ጠቃሚ መድረክ ነው ሲሉ ተ
ናግረዋል፡፡
አቶ አረጋ ዘሩ የዕቅድ ክትትልና
ግምገማ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተ
ር በተቋሙና በህዝብ ክንፉ በጋራ
የታቀደውን የእቅድ አፈጻጸም ሪ
ፖርት በጽሁፍ ያቀረቡ ሲሆን የ
ተወሰኑ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም
አብዛኛዎቹ ስራዎች በሂደት  ላይ
መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡
በአቶ አበበ በቀለ የስረአተ ጤና
ምርምር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተ
ር በኩል ደግሞ ተላላፊ ያልሆኑ
በሽታዎች ላይ የተዘጋጀ ጥናታዊ
ጽሁፍ የቀረበ ሲሆን ምንነታቸው
ላይና መንስኤያቸው ምን እንደሆ
ነ ከመዘርዘሩም በላይ ጥናቱ በሆስ
ፒታሎችና በጤና ጣቢያዎች ላይ

> ....ሊሳካ የሚችለው በህዝ
> ብ  እና በተቋማት መካ
> ከል ጥብቅ የሆነ ግንኙነ
> ት ሲኖር ነው በመሆኑ
> ም ኢንስቲትዩታችን  የ
> በለጠ ውጤታማ እንዲሆ
> ን የዛሬውን .....

ትኩረት ተደርጉ እንደተጠና  በዝ
ርዝሩ ቀርቧል፡፡
አቶ ተመስገን አወቀ ከምግብ ሳይ
ንስና ኒውትሪሽን ዳይሬክቶሬት በ
በኩላቸው ለስኳር ህመምተኞች የ
ተዘጋጀ የአመጋገብ ማንዋል ያቀ
ረቡ ሲሆን ህመምተኞቹ በምግብ
ና በህክምና እንዴት ህመሙን መ
ቆጣጠር እንደሚችሉ በዝርዝር እ
ና በስፋት አቅርበዋል፡፡
በቀረቡት ጽሁፎች ላይ ዶክተር
ይበልጣል  አሰፋ የኢንስቲትዩቱ
ምክትል ዋና ዳይሬክተር ያወያዩ
ሲሆን ከውይይቱ ተሳታፊዎች  በ
ቀረበው ሪፖርትና ጥናታዊ ጹሁ
ፎች ላይ መቀነስና  መጨመር ያ
ለባቸውን ሳይንሳዊ ሃሳቦች በጥል
ቀት ሃሳባቸውን ከመስጠታቸውም
በላይ ግልጽ ያልሆኑ ሃሳቦችንም
እንዲብራራላቸው ጠይቀዋል፡፡
ም/ዋና  ዳይሬክተሩ  በማጠቃለያ
ንግግራቸው  እንደገለጹት  በመድ
ረኩ የቀረቡት የውይይት ሃሳቦች
ና አስታያየቶች እጅግ ገንቢና ጠ
ቃሚ ናቸው በቀጣይም እየገመገ
ምንና እየፈተሸን እንሄዳለን መድ
ረኩም  በጣም  ጠቃሚ ስለሆነ ቀ
ጣይነት ሊኖረው ይገባል በመሆኑ
ም በቀጣይ መድረካችን ሁላችን
ም የ2009 ዓ.ም እቅዳችንን ይዘን
ስለምንመጣ የተሻለ መድረክ ይሆ
ናል ስለዚህ የበለጠ በጋራ እንሰራ
ለን በማለት የእለቱን መድረክ አ
ጠቃለዋል፡፡

## . .ጤናማ አመጋገብን ለማሻሻል

ከገጽ 2 የዞረ



ፊቻ ንግግር ያደረጉት አቶ አቤል የሻነህ የኢንስቲትዩቱ የህዝብ ግንኑነት ሃላፊ ሲሆኑ በንግግራቸው ወቅት ለሰልጣኞች እንደገለጹት በኢትዮጵያ የተመጣጠነ ምግብ ያለመኖር ችግርን ለመቅረፍ ሃላፊነቱን ወስዶ እየሰራ ያለው የኢትዮጵያ የህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ነው፡፡

በመሆኑም ለዚህ ታላቅ ሃገራዊ አላማ የሚሰበሰበው መረጃ ታአማኒነትና ጥራት ያለው ሊሆን ይገባል ስለዚህ የሚገጥማችሁን የተላያዩ ፈተናዎች በማለፍ የተጣለባችሁን ሃላፊነት በአግባቡ እንድትወጡ እና የምትሰበስቡት መረጃ ውጤታማ እንዲሆን አሳስባለሁ ብለዋል፡፡

አቶ ተስፋዬ ሐይሉ የምግብ ሳይንስና ኒውትሪሽን ምርምር ዳይሬክቶሬት ተጠባባቂ ዳይሬክተር በኩላቸው እንደገለጹት በኢትዮጵያ የተመጣጠነ ምግብ ያለመኖር ችግር ስር የሰደደ ሲሆን ይህም ሊሆን የቻለው የአመጋገብ ባህላችን በእህል ተዋጽኦ ላይ ያተኮረ ከመሆኑም በላይ የእንስሳ እና የፍራፍሬ ተዋጽኦ አመጋገባችን ደግሞ በጣም ዝቅተኛ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ሃላፊው አያይዘው እንደገለጹት በምግብ ያለመመጣጠን ችግር ምክንያት ለሚመጡ ችግሮች በሃገራችን እየሰፋ እንዳይመጣ ከወዲሁ ለመቅጨት ያስችል ዘንድ ይህ የዳሰሳ ጥናት በሃገር አቀፍ ደረጃ ተጀምሯል ሰልጣኞችም በመረጃ አሰባሰብ ዙሪያ ማወቅ ያለባቸውን እየሰለጠኑ ይገኛሉ ብለዋል፡፡

## . .ጡረተኞች ማህበር ተመሰረተ

ከገጽ 3 የዞረ



ተቋሙን ለመርዳት ታስቦ የተመሰረተ ማህበር ነው ብለዋል፡፡

አቶ አሰፋ አያይዘው እንደገለጹት ጡረታ የወጡት ባለሞያዎች በራሳቸውና በቤተሰባቸው ላይ የሞት አደጋ ወይም ከባድ ችግር ሲደርስ ለመረዳዳትና ለመተሳሰብ ጭምር ታስቦ የተመሰረተ ማህበር ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ማህበሩ የመተዳደሪ ደንብ በማውጣት አራት አባላት ያሉት ኮሚቴ ያቋቋመ ሲሆን ከኢንስቲትዩቱ የድጋፍ ደብዳቤ ለክፍል ከተማ ማኅበራት ማደራጃ የሚላክ ሲሆን ህጋዊ ፈቃድ ካገኘ በኋላ ወደተቋቋመበት ዋና አላማ የሚገባ መሆኑን ከማህበሩ አባላት ተገልጿል፡፡

በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 11 ላይ በተቀመጠው መሰረት የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አመሃ ከበደ የማህበሩ የክብር ፕሬዝደንትና የበላይ ጠባቂ ሆነው ተመርጠዋል፡፡

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር ዶክተር አመሃ ከበደ በበኩላቸው ማህበሩን አስመልክቶ እንደገለጹት የኢንስቲትዩቱን ጡረተኞች ማህበር ከኢንስቲትዩታችን የሚፈለገውን ድጋፍ አቅም በፈቀደ መጠን ደረጃ በደረጃ ለማሟላት ጥረት እናደርጋለን ነገር ግን በማህበሩ በኩል የቅድሚያ ትኩረት የሚሹትን ጉዳዮች በመለየት ማቅረብ ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

ዋና ዳይሬክተሩ ጨምረው እንደገለጹት ማህበሩ በቀጣይ ወደ ጡረታ ለሚገለሉ የኢንስቲትዩታችን ሰራተኞች ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ እና ጠንካራ ማህበር ለመጀመር በርትቶ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡